SEATTLE PUBLIC SCHOOLS

# የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች
# የአድልዎ ቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ

**የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች በጾታ:በእምነት:በመልክ:በሃይማኖት: በዘር ሃረግ: በትውልድ አካባቢ: በእድሜ:በኢኮኖሚ ሁኔታ:በጾታ:በ እርግዝና: በጋብቻ ሁኔታ: በሰውነት አቋም : በስሜት ህዋስ: የአእምሮ ወይም የአካል ጉድለት: በክብር የተሰናበተ ወታደር ወይም የውትድርና ሁኔታ ወይም በሰለጠነ ውሻ ወይም እንሰሳ አገልግሎት በማግኘት ላይ መሰረት ያደረገን አድልዎ ይከለክላል::**

***አድልዎ ማለት ምን ማለት ነው?*** **አድልዎ ማለት ተገቢ ወይም ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ የአንድ የተጠበቀ ክፍል አካል በመሆናቸው ምክንያት የሚደርስ በደል ማለት ነው:: አድልዎ ሰዎች የአንድ የተጠበቀ ክፍል አካል በመሆናቸው ለየት ባለ መንገድ ማስተናገድ ወይም በአንድ ፕሮግራም ላይ እንዳይሳተፉ: አገልግሎት እንዳያገኙ: ወይም ስራ ላይ እንዳይሳተፉ ወይም አካል ጉዳተኛ በመሆናቸው አለመቀበልን ያካትታል:: የአድልዎ ጥቃት በተጠበቀ ክፍል ላይ በቃል ወይም በአካል የሚፈጸም ጥቃት ነው::**

***የተጠበቀ ክፍል ማለት ምን ማለት ነው?*** **የተጠበቀ ክፍል ማለት የተወሰኑ ነገሮችን የሚጋሩና የፌዴራል:የክልልና የአካባቢ ህግ ከአድልዎና ጥቃት ጥበቃ የሚያደርግላቸው የሰዎች ቡድን ማለት ነው::በሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች ጥበቃ የሚደረግላቸው ቡድኖች ከላይ በጾታ በዘርና በመሳሰሉት ከአድልዎ ነጻ መሆናቸው የተገለጹትን ማለት ነው::**

***አድልዎን በተመለከተ እንዴት ቅሬታ ማቅረብ እችላላሁ?*** **እርስዎ ወይም ልጅዎት አድልዎ ወይም ጥቃት በት/ቤት ውስጥ ደርሶበታል ብለው የሚያምኑ ከሆነ በህጋዊ መንገድ ቅሬታዎን የማቅረብ መብት አልዎት:: ይህ ቅጽ አስፈላጊ ባይሆንም: ሁሉም ቅሬታዎች (ሀ) በጽሁፍ (ለ)በቅሬታ አቅራቢው መፈረምና (ሐ)በትክክል የተፈጸመውን ድርጊት: ሁኔታውን: አድልዎ መኖሩን የሚያሳየውን ሁኔታ በትክክል ማሳየት ይኖርባቸዋል::**

**ቅሬታውን ከማቅረብዎ በፊት ጉዳዩን ከልጅዎት ት/ቤት ርዕሰ መምህር ጋር ወይም ከሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች ቅሬታ ሰሚ ጋር በ(206) 252-0529 ሊነጋገሩ ያስፈልጋል::**

**ቅሬታውን የማቀርበው የት ነው? ለተማሪዎች:ወላጆች/አሳዳጊዎች እና የህብረተሰቡ አባላት ጥያቄዎች እና/ወይም ለተባለው አድልዎ ጾታዊ ጥቃትን ጨምሮ ቅሬታው ለተማሪዎች የሲቪል መብት ቢሮ:የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች MS 32-149, P.O. Box 34165, Seattle, WA 98124-1166; ኢሜል:oscr@seattleschools.org ወይም በስልክ 206-252-0306 ማቅረብ ይቻላል::**

**ለሰራተኞች ጥያቄዎች እና/ወይም ለተባለው አድልዎ ጾታዊ ጥቃትን ጨምሮ ቅሬታው ለሰው ልማት ሃይል አስተዳደር ምክትል ሱፐርኢንቲንደንት የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች MS 33-157, P.O. Box 34165, Seattle, WA 98124-1166; email: hreeoc@seattleschools.org; ወይም በስልክ 206-252-0024 ማቅረብ ይቻላል::**

**የቅሬታዬ ሚስጢራዊነት ይጠበቃል? ሚስጢራዊነቱ አስተማማኝ ላይሆን ይችላል:: የተፈጸመውን የአድልዎ ቅሬታ ከማጣራት አኳያ የቅሬታ አቅራቢውን ወይም የተማሪውን ማንነት ይፋ ማድረግ ያስፈልግ ይሆናል:: በተቻለ መጠን ግን የተሰጠውን መረጃ ለምርመራዉ ያስፈልጋሉ ለምንላቸው ሰዎች ብቻ በማካፈል ሚስጢራዊነቱን ለመጠበቅ ጥረት እናደርጋለን:: በቀረበው የቅሬታ ጉዳይ ላይ የወረዳው ት/ጽቤት መረጃውን የአድልዎ በደሉን ላደረሰው ለማሳወቅ አስፈላጊውን ፕሮሰስ/ሂደት መከተል ይጠበቅበታል:: ስለሆነም ለተከሳሹ የማይነገሩ ሁኔታዎች በጉዳዩ ላይ የምንሰጠውን ምላሽ: የምርመራ ሂደት:የቅሬታውን ሁኔታ የምንፈታበትን ሁኔታ ሊገድብብን ይችላል:: ይፋ የማይሆኑ ቅሬታዎች በወረዳው ት/ጽ/ቤት የአድልዎ ቅሬታ አሰራር መሰረት መደበኛ እንዳልሆኑ ቅሬታዎች ይታያሉ::**

**መበቀል የተከለከለ ነው? አዎን:: ማንኛውም ሰው በቀረበበት ቅሬታ ምክንያት ለመበቀል መሞከር ህጋዊ ካለመሆኑም በላይ የወረዳውን ፖሊሲ የሚጻረር ነው:: ወረዳው የቅሬታ አቅራቢዎችንና የምስክሮችን ደህንነት ከመጠበቅ አኳያ ሙሉ በሙሉ ጸረ-ብቀላ የሆኑ አፈጻጸሞችን ተግባራዊ ያደርጋል::**

## ***መመሪያዎች:***

**እባክዎትን ቅሬታውን በተመለከተ በጽሁፍ የተዘጋጀና ፊርማዎት ያለበትን አቤቱታ ያቅርቡ ወይም ይህንን ቅጽ ይሙሉ:: ያጋጠመዎትን ሲገልጹ በተቻለ መጠን እያንዳንዱን ነገር ያብራሩ:: ቀን: ያጋጠመውን ነገር: ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሰዎች ስም: እና ስለ ሁኔታው የሚመሰክሩ ሰዎችን ስም ዝርዝር: ያካትቱ:: የቅሬታዎት ጽሁፍ ባለው ቦታ ሊገደብ አይገባም:: የማጣራት ሂደቱን ሊረዱ የሚችሉ ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎችን እንዲያያይዙ ይበረታታሉ::**

**ቅሬታዎትን: ለት/ቤቱ ርእሰ መምህር ወይም በኢሜል ለ: OSCR@seattleschools.org ወይም በእጅ ለ: Seattle Public Schools, 2445 3rd Ave. S, Seattle, WA 98134 ወይም በፖስታ ለ: Office of Student Civil Rights, MS 32-149; P.O. Box 34165, Seattle, WA 98124-1165 ይላኩ::**

**I የግል መረጃ (እባክዎትን ይሙሉት):**

**ስምዎት:** ____________________________________________

**ስልክ ቁጥር: (የቤት)**____________________________**(የስራ/ሞባይል)** ______________________

**ኢሜል:** ____________________________________________

**የቤት አድራሻ:** ____________________________________________

*መንገድ* *ከተማ* *ዚፕ*

**( ) ሰራተኛ ( ) ተማሪ**

**( ) ወላጅ/አሳዳጊ በተማሪው ምትክ**

**( ) ሌላ ሰው**

II. **የቅሬታው ዓይነት (የሚመለከተው ላይ ሁሉ ምልክት ያድርጉ)::**

**( ) አድልዎው የተመሰረተው:**

**( ) በጾታ ( ) በጾታዊ ጥቃት ( ) ሌላ ዓይነት ጥቃት**

**( ) ዘር ( ) መልክ ( ) ሃይማኖት ( ) የትውልድ ቦታ ( ) አካል ጉዳተኛነት**

**( ) የኢኮኖሚ ሁኔታ ( ) ጾታ(Gender) ( ) የጾታ ፍላጎት ( ) የጾታ ማንነት**

**( ) እርግዝና ( ) የጋብቻ ሁኔታ ( ) የሰውነት አቋም ( ) የእንስሣት አገልግሎት መጠቀም**

**( ) እድሜ ( ) የውትድርና ሁኔታ ( ) የዘር ሃረግ**

**( ) ብቀላ**

III. **አድልዎው/በደሉ/ጥቃቱ/ብቀላው የተፈጸመበት ቀን:**

**ቆየት ያለ** ____________________

**በቅርብ** ____________________ **ወይም ( ) እየቀጠለ ያለ ተግባር**

**IV. አድልዎውን/በደሉን/ጥቃቱን/ብቀላውን የፈጸመው ሰው/ሰዎች:**
**(አስፈላጊ ከሆነ ተጨማሪ ገጾችን ይጠቀሙ)**

**ስም:** ____________________________________________

**ት/ቤት/የስራ ክፍሉ:**____________________________________________

**ስም:** ____________________________________________

**ት/ቤት/የስራ ክፍሉ:**____________________________________________

**ስም:** ____________________________________________

**ት/ቤት/የስራ ክፍሉ:** ____________________________________________

**V. ቅሬታዎት:**

**እባክዎትን በክፍል IV ላይ ስሙ በተጠቀሰው ሰው ላይ የሚያቀርቡትን ቅሬታ ያብራሩ:: በተለይ እርስዎ ወይም ልጅዎት ላይ የጾታ ጥቃት እንዴት እንደደረሰብዎት? ባህሪውን: አስተያየቶችን: ወይም ክስዎን እንዲያቀርቡ ያደረግዎትን ነገር ያብራሩ:: አስፈላጊ ከሆነ ተጨማሪ ገጾችን ያያይዙ::**

VI. ***እባክዎትን ጉዳዮትን ሪፖርት ያደረጉላቸውን የወረዳውን የአስተዳደር ሰራተኛች እንደ ርዕሰ መምህር ወይም ምክትል ር/መምህር ይግለጹ*:**

***ሪፖርት ያደረጉለት ሰው ስም:*** ______________________ ***ቀን:*** ______________________

**ጉዳዮትን እንዴት እንደገለጹ ያብራሩ:**

**ውጤቱ:**

***ሪፖርት ያደረጉለት ሰው ስም:*** ______________________ ***ቀን:*** ______________________

**ጉዳዮትን እንዴት እንደገለጹ ያብራሩ:**

**ውጤቱ:**

***ሪፖርት ያደረጉለት ሰው ስም:*** ______________________ ***ቀን:*** ______________________

**ጉዳዮትን እንዴት እንደገለጹ ያብራሩ:**

**ውጤቱ:**

VII. **በክፍል V ላይ እንደተመለከተው በጉዳዩ ላይ እዉቀት ያላቸው ሰዎች**:
**(*እነዚህ ሰዎች በጉዳዩ ላይ ምስክር የሚሆኑ ወይም ስለሁኔታው እዉቀት ያላቸው ናቸው:: ተጨማሪ ስሞችን ማያያዝ ይቻላል::*)**

**ስም:** ______________________ ***ለርስዎ ያለው ዝምድና*** ______________________
***ጓደኛ: ተማሪ: አስተማሪ: የመሳሰሉት***
**ስልክ ቁጥር:** ______________________ ***ኢሜል:*** ______________________

**ስም:** ______________________ ***ለርስዎ ያለው ዝምድና*** ______________________
***ጓደኛ: ተማሪ: አስተማሪ: የመሳሰሉት***
**ስልክ ቁጥር:** ______________________ ***ኢሜል:*** ______________________

**ስም:** ______________________ ***ለርስዎ ያለው ዝምድና*** ______________________
***ጓደኛ: ተማሪ: አስተማሪ: የመሳሰሉት***
**ስልክ ቁጥር:** ______________________ ***ኢሜል:*** ______________________

*VII.* **የቀጠለ**

*ስም:*____________________________________*ለርስዎ ያለው ዝምድና* _________________________________

*ጓደኛ: ተማሪ: አስተማሪ: የመሳሰሉት*

**ስልክ ቁጥር:**____________________________**ኢሜል:** ______________________________________________

**VIII.** ***የሚያስፈልገው የማስተካከያ እርምጃ:***

***ወረዳው ቅሬታውን በምን መልኩ እንዲፈታው ይፈልጋሉ?***

# ተጨማሪ መረጃ

የተማሪዎች ሰብአዊ መብት ቢሮ ወይም ከነርሱ ጋር ያለው አጣሪ ክፍል መፍትሄውን ከመፈለግ አኳያ ከቅሬታው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች ያጣራል: እንዲሁም እርስዎንና በቅሬታዎ ውስጥ ያካተቱዋቸውን ሰዎች ቃለ መጠይቅ ያደርጋሉ:: የወረዳው ት/ጽ/ቤትም በራሱ በኩል በምርመራው ሂደት ውስጥ ሌሎችንም ያነጋግራል::

ሚስጢራዊነቱ አስተማማኝ ላይሆን ይችላል:: በተቻለ መጠን ግን የተሰጠውን መረጃ ለምርመራዉ ያስፈልጋሉ ለምንላቸው ሰዎች ብቻ በማካፈል ሚስጢራዊነቱን ለመጠበቅ ጥረት እናደርጋለን::በቀረበው የቅሬታ ጉዳይ ላይ የወረዳው ት/ጽቤት መረጃውን የአድልዎ በደሉን ላደረሰው ለማሳወቅ አስፈላጊውን ፕሮሰስ/ሂደት መከተል ይጠበቅበታል:: ማንነትዎ ለተከሳሽ ይፋ እንዳይሆን የሚያቀርቡት ጥያቄ ወረዳው ውጤታማ ምርመራ እንዳያደርግና የምርመራውን ሂደት በመገደብ ቅሬታዎ እርስዎ በሚፈልጉት ደረጃ መፍትሄ እንዳያገኝ ያደርጋል::

ቅሬታውን በማቅረብዎት ወይም በምርመራው ሂደት ውስጥ በተሳተፉ ሰዎች ላይ በቀል ማድረስ መሞከር ህጋዊ ካለመሆኑም በላይ የወረዳውን ፖሊሲ የሚጻረር ነው:: ቅሬታዎን በማቅረብዎ ምክንያት በቀል የሚያጋጥምዎት ከሆነ እባክዎትን የት/ቤቱን ርዕሰ መምህር ወይም የተማሪዎች ሰብአዊ መብት ቢሮን ውድያውኑ ያነጋግሩ::

ይህን ቅሬታ ከማቅረብዎ በተጨማሪ ከውጫዊ ድርጅት ማለትም ከህግ አስከባሪ ድርጅቶች: ከዋሽንግተን የህዝብ ት/ቤቶች ሃላፊ: ወይም ከዩ. ኤስ የትምህርት ዲፓርትመንት እና ከሰብዓዊ መብቶች ቢሮ ዘንድም ቅሬታዎትን የማቅረብ መብት አልዎት:: ቀደም ሲል ተመሳሳይ ቅሬታ ለሌላ አካል ወይንም ለፍ/ቤት አቅርበው ከሆነ ወረዳው የርሱ ውጤት እስኪታወቅ ድረስ ምርመራውን ወደ ሌላ ጊዜ ያስተላልፋል::

የቅሬታ አቀራረብ ሂደት በዚህ ድህረ ገጽ ላይ ተቀምጧል:: https://www.seattleschools.org/UserFiles/Servers/Server_543/File/District/Departments/Office%20of%20Student%20Civil%20Rights/Discrimination%20Complaint%20Procedures%20(Aug31%202015).pdf

የቅሬታ አቀራረብ ሙሉ ሂደት በዚህ ድህረ ገጽ ላይ ተቀምጧል:: http://www.seattleschools.org/UserFiles/Servers/Server_543/File/District/Departments/School%20Board/Procedures/Series%203000/3210SP.B.pdf

## ማረጋገጫ

ይህንን ቅሬታ አስመልክቶ ያቀረብኩት መረጃና ማስረጃዎች በሙሉ እውነተኛ እና ትክክለኛ መሆናቸውን አረጋግጣለሁ:: አውቆ የተሳሳተ መረጃ መስጠት ወይም እውነት ስለመሆኑ የማላምንበትን መረጃ በዚህ ቅሬታ ውስጥ ወይም በምርመራ ሂደቱ ውስጥ ማካተት በወንጀል የሚያስጠይቀኝ መሆኑን አረጋግጣለሁ::

የዚህ ቅሬታ ሚስጢራዊነት አስተማማኝ ሊሆን እንደማይችል እና ቅሬታው ላይ ምርመራ ለማድረግ የኔ ወይም የልጄ ማንነት ለተከሳሽ ወይም ለሌሎች ይፋ ሊሆን እንደሚችል ተገንዝቤያለሁ::

ፊርማ:________________________________________ ቀን: ________________________________

ይህንን ለት/ቤቱ ርእሰ መምህር ወይም በኢሜል ለ: OSCR@seattleschools.org ወይም በእጅ ለ: Seattle Public Schools, 2445 3rd Ave. S, Seattle, WA 98134 ወይም በፖስታ ለ: Office of Student Civil Rights, MS 32-149; P.O. Box 34165, Seattle, WA 98124-1165 ይላኩ::

**———————————በወረዳው ተወካይ የሚሞላ———————————**

Name and Title: ______________________________________ Date received: ______________

Date provided to Office of Student Civil Rights:_________________by (method of delivery) _______________

Date received by Office of Student Civil Rights: ____________________

Assigned for investigation to________________________________on _____________

Signed: ______________________________________________________________